የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21st Year No. 52
ADDIS ABABA, 31st July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፰/፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮንጎ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የጠቅላላ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ...................ገጽ ፰ሺ፪፻፷፰

**CONTENTS**

Proclamation No. 898/2015

General Co-operation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Congo Ratification Proclamation...............................Page 8268

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፰/፪ሺ፯

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮንጎ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን የጠቅላላ ትብብር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮንጎ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የጠቅላላ ትብብር ስምምነት ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም በብራዛቢል የተፈረመው በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No. 898/2015

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE GENERAL CO-OPERATION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF CONGO**

WHEREAS, the General Co-operation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Congo, was signed in Brazzaville on the 16th day August, 2010;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 25th day of June 2015;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows፡

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80,001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮንጎ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገ የጠቅላላ ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፰/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኮንጎ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ነሐሴ ፲ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ብራዛቢል የተፈረመ የጠቅላላ ትብብር ስምምነት ጸድቋል፡፡

**፫. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይህንን ስምምነት ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስድ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "General Co-operation Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Congo Ratification Proclamation No. 898/2015''.

**2. Ratification of the Agreement**

The General Co-operation Agreement signed in Brazzaville on the 16th day of August, 2010 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Congo, is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Foreign Affairs**

The Ministry of Foreign Affairs is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July , 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**